የቴዎድሮስ አሟሟትና የመቅደላው ዘረፋ

ግርማ ኪዳኔ

የመጨረሻው የመቅደላ ግብግብ ሰኞ ሚያዚያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም. ወደማቆሙ ተቃረበ። የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ቴዎድሮስን አድኖ ለመያዝ በየአቅጣጫው መሺሺጥ ጀመረ። የቴዎድሮስን ሁኔታ አስመልክቶ የኒውዮርክ ታይምስ ሪፖርተር እስታንሊ(1) ሲናገር ሰኞ ከቀኑ አሥር ሰዓት አካባቢ እንግሊዝ በመቅደላ ላይ ካሠማራቻቸው ወታደሮች መካከል ሁለት የአይሪሽ ወታደሮች የተኩስ ድምጽ ወደሰሙበት አቅጣጫ እየተክለፈለፉ እንደደረሱ፤ አንድ ያልታወቀ ኢትዮጵያዊ ከመሬት ላይ ተዘርሮ ለመሞት በማጣጣር ላይ እንደለ ያገኙታል። የግለሰቡ ጣር ስሜት ሳይሰጣቸው ቀድሞውንም ከኛ የተሰረቀ ነው በማለት በቀኝ እጁ አቅጣጫ የወደቀውን ሽጉጥ አንስተው ይወስዱበታል። ይህ አልበቃ ብሎአቸው የጣቱን የወርቅ ቀለበትና የአንገቱን የወርቅ መስቀል ይዘርፉታል።(2) ከዚያም የወሰዱትን ሽጉጥ እያገላበጡ በማድነቅ ሲመለከቱ ከጉን በኩል ከብር ተቀርጾ የተለበደ ጽሑፍ ያገኙበታል። ጽሑፉም፡«እንደ ኤ.አ. 1854 ለአሽከሬ ለፕላውደን የአቢሲኒያው ንጉሥ ቴዎድሮስ ለደረጉለት ቅንነት የተመሳበት ደግነት ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ከታላቋ ብሪታንያና የአይርላንድ ንግሥት ቪክቶሪያ የተላከ ስጦታ» የሚል ነበር።(3)

ወታደሮቹ ጽሑፉን ከነበቡ በኋላ ከነከናቸው። አንደኛው ወታደር ቴዎድሮስ ይሆን እንዴ?(4) በማለት ነፍሱ ልትወጣ የተቃረበውን ግለሰብ ማስተዋል ጀመረ። ምናልባትም ወታደሮቹ ሊለዩአቸው ያልቻሉበት ሌላው ምክንያት አጼ ቴዎድሮስ በጠለት መወረራቸውን እንደተረዱ ከቤተሰቦቻቸውና ከቅርብ ተከታዮቻቸው ጋር ተሰናብተው በሽጉጥ እራሳቸውን መተው እንደወደቁ ጠላቶቻቸው እሳቸው መሆናቸውን እንደይለዩአቸው በማሰብ ወልደ ጋብር የሚባለው የቤት አሽከራቸው የሚደርቧትን ባለቀጭን ጥለት ነጠላቸውንና ታጥቀውት የነበረውን ባለከፋይ ቀበቶአቸውን አውልቆ በመውሰድ ቁጥራቸው አስራአምስት ያህል ከሚሆን ከቴዎድሮስ ጭፍሮች ጋር በማምለጥ ተሸሽጎ እንደነበር ለእንግሊዝ አፈሰሮች በሰጠው ቃለመጠይቅ ላይ

ተጠቅሷል።(5) ሌላው ቴዎድሮስ መሆናቸው ያልታወቀበት ምክንያት አለበበሳቸው ተራ ኢትዮጵያዊ ከሚለብሰው ልብስ የተለየ በለመሆኑ ነበር። በተለይም በደ እግራቸውን ያለጫማ መታየታቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከደረታቸው ስፋትና ከትከሻቸው ትልቅነት በሰተቀር ቁመታቸው መከለኛ እንጂ ረዥምና ግዙፍ በለመሆኑ፤(6) እኒያ በሀገራቸው ላይ ተነስተውበቸው የነበሩትን ሽፍቶች ከመደምሰስ አልፈው ተርፈው በጀኔራል ናፒየር የሚመራውን ዘመናዊ የእንግሊዝ ጦር እጁን አልሰጥም በማለት በድንገት የወደቁ ታሳቅ እንበሳ መሆናቸውን ከቶውንም ለማመን አልቻሉም ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ መቅደሰ በእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ቁጥጥር ሥር ሆነች። ቀደም ሲል የቴዎድሮስ እስረኞች የነበሩትም ኢትዮጵያውያን በግርግር የታሰሩበትን ቤት በመስበር የእግር ብረታቸውን መሬት እየጎተቱ በአደበባይ መታየት ጀመሩ።(7) ከፊሉም እንግሊዘኞች ወደሰፈሩበት ከምፕ በመሄድ ተቀለቀሉ።

ወዲያውኑ አንድ ግለሰብ እየሮጠ ሄደ የጀኔራል ናፒየር የቅርብ ረዳት ለነበረው ለሰር ቻርልስ እስቴቨሊ «እዚያ አንድ ግለሰብ ተዘርሯል፤ ሰዎች ቴዎድሮሰ ነው ይላሉ፤»(8) በማለት ሪፖርት ያቀርባል። እስቴቨሊ ግን በነገሩ ሙሉ በሙሉ አለመነበትም ነበር። በዚህም ምክንያት ይህ ግንኙቱ ያልታወቀውን ራሰ በቃሬዛ ላይ በማድረግ አምጥቶ ለማሰየት በማሰብ ግለ ሰቡ ራሰው ወደ ነበረበት ሥፍራ ተመልሰ ሄደ። ጭካኔ በተመለበት አኪኋን ሁለት እግሮቻቸውን በመጎተት ለቃሬዛ መሸከሚያ ተብሎ ከተሠራው የእንጨት ርብራብ ላይ እንደጣሉአቸው ሦስት ጊዜ ከቃሰቱ በኋላ ህይወታቸው ልታልፍ ችለች።(9) ይህንን ድርጊት አስመልክቶ ማርከሀም ሲያብራራ «ወታደሮቹ የአጼ ቴዎድሮስን ቃሬዛ ተሸክመው ለሰርቻርልስ ለማሰየት እንደደረሱ ታሰረው የተፈቱት አስረኞች በመሽቀደደም መጀመሪያ መልካቸውን አተኩረው ከዩ ሰኋለ አንድ ነገር ትዝ አለቸውና የግራ እጃቸውን ከፍ አድርገው ጣታቸውን ማየት እንደጀመሩ አንደኛው ጣታቸው ሰበራ(10) ሆና አገኙት። አጼ ቴዎድሮስ ገና በወጣትነታቸው ዘመን ጎጃም ለይ በጥይት ጣታቸው ለይ ተመተው(11) ስለነበር የተቆረጠውን ጣት ስለዩ፤ ቴዎድርስ መሆናቸውን አረጋገጡ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ራሰው የአጼ ቴዎድሮስ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ በእንግሊዝ የጦር መኩንኖች ዘንድ አጠራጣሪ ስለመሰለ አጼ

ቴዎድሮስ በሕይወት ሰሉ የሚያውቃቸው የነበረው ራሰም መጠቶ እንዲያያቸው ተደረገ።(12) ብዙ ሰይቶይ ራሰም ወዲያው እየሮጠ መቶ ሲያያቸው አጼ ቴዎድሮስ ሆነው አገኛቸው። ምንም እንኳ በሱና በአጼ ቴዎድሮስ መካከል አልፎ አልፎ አለመግባባት ቢፈጠ»ርም ቶራጥ መሪ መሆናቸውን ጠንቅቶ ያውቅ ስለነበረ ሁኔታውን እንደተመለከተ መንፈሱ ተረበሸ። በተለይም ከመሞታቸው በፊት የተናገሩት ቃል ትዝ አለው። ይኸውም «እንድ ቀን እኔ ስሞት ታየኝ ይሆናል፤ ከዚያም በራሰዬ ላይ ቆመሀ ይህን ደካማ ሰው በመቅበር ፋንታ ከሚደው ላይ እንደወደቀ በሰብሰ መቅረት አለበት በማለት ትረግመኝ ይሆናል»(13) ብለው የተናገሩት ትዝ አያለው በሀዘን ተውጦ ይታይ ነበር።

የአጼ ቴዎድሮስ መሞት በይፋ እንደታወቀ የእንግሊዝ ወታደሮች ደስታ በተመለበት ሁኔታ በንዲራቸውን በግውለብለብ በመቅደሰ ተራራ ላይ ጨኽታቸውን አስተጋቡት።(14) ብሔራዊ መዝሙራቸውንም አሰሙ።(15) በቴዎድሮስ እጅ ታስረው የነበሩትም አስረኞች ሟቹ ራሰ አከባቢ የፈንጠዝያ ግብዣ ለማድረግ ከያሉበት ተጠራሩ።(16) የሟቹንም ገጽታ ለማየት የሚጎርፈው ሕዝብ ብዛት እየጨመረ መጣ፤ ሕዝቡም ራሰውን በደንብ ለማየት እንዲችል ወደሚደ ተጎትቶ ተቀመጠ።(17) ዙሪያውንም በመከበብ ርቃነ ሥጋቸው አስኪታይ ድረስ የለበሱትን ልብስ ከብዙ በታ ተለተሉት።(18)

በወቅቱ የአይን ምስክር በመሆን ያረጋገጠው አሜሪካዊ ሪፖርተር ህይወታቸው ስለለፈችው የመቅደለ ጀግና ሲያብራራ የተለየ ክብር ሰይደረግለቸው፤ «ጠበቂ ዘብ በእጠገበቸው ሰይቶም፤ በቃሬዛ ላይ ለብዙ ሰዓት ያህል ከመሬት ተዘርረው፤ ፀጉራቸው ተሸልቶ፣ ልብሰቸው ተገፎና ተቀዳደ ከፈል እርቃነሥጋቸውን በማየቴ የቀድሞው ቴዎድሮስ መሆናቸው አጠራጠረኝ» ይልና፤«ራት ብዬ ስመለከት ብዙ እፈሰሮች በደም የተበከለውን የቴዎድሮስን ሽሚዝ ለኔ ይገበኛል በማለት ሲጋተቱና ሲጣሉ ተመልከቼ ነበር።»(19) ብሎ ንግግሩን ይደመድማል።

ስለሆነም በዚያን ጊዜ ቴዎድሮስ ሲነግሱ ለብሰውት የነበረው የክብር ልብስና በእንጻሩ ደግሞ ከሞቱ በኋላ የተወሰደባቸው በደም የተበከለችው ሽሚዝ በእንግሊዝ አገር ራት በለ ሰሜናዊ ክፍል «በንክ ፊልድ ሙዚየም» ሀሊፋክስ ዩክሼር ተብሎ በሚጠራው መዘክር ውስጥ

ሲገኝ የተሸለተው ፀጉራቸው ግን ለንደን ከተማ ናሽናል ወር ሙዚየም ውስጥ እንግሊዘኞች እጉል ጀብደኝነታቸውን ለማስታወስ ብለው አስቀምጠውታል።

ይህንን አስነኖሪ ድርጊት ያስተዋለ አንድ ታዛቢ የቴዎድሮስ ሬሳ ከፈል ርቃኑን ስለነበረ የሰው መሰቂያ ሆኖአል በማለት ለናፒየር ተናገረ።(20) ናፒየር ግን የተሠራው አስነዋሪ ሥራ አንድ ወታደር ከሚያደርገው የዲሲፒሊን ስነሥርዓት አሠራር ውጪ መሆኑን እየተገነዘበ አንዳችም የቅጣት እርምጃ ሳይወስድ ቃሬዛው እንዲሰብስና በማግስቱ ለቀብር እንዲዘጋጅ የሚል ትዕዛዝ ሰጠ።(21) ሆኖም ይህ ከመፈጸሙ በፊት በስዕል መልክ ፎቶግራፍ እንዲነሱ ተደረገ። ከመጣበት ተልእኮ ሌሳ በስዕል በመሰል ልዩ ሙያ የነበረው የብሪትሽ ሙዚየም ተወካይ ሪቻርድ ሆምስ(22) በደረቅ እርሳስና ብሩሽ እግከይነት ስሎ አቀረበ። የሰለውም ስዕል ትክክለኛውን የቴዎድሮስን መልክ የያዘ እንደነበረ የቴዎድሮስን አሟሟት ለመመርመር ከተገኘው ሀኪምና በሚስተር ራሰም ተረጋገጠ።(23) ከዚያም በኋላ ቀደም ሲል ጠቅለይ የጦር አዛዡ እንደዘዘው ሁሉ በሚስተር ራሰም አማካይነት ቃሬዛው ከስፍራው ተነስቶ የእንግሊዝ አስረኞች ይኖሩበት ከነበረው ገቢ ፒትር ተብለ ከምትጠራው ጎጀ(24) ውስጥ ለቀብር እንዲዘጋጅ ተደረገ።

የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ከመፈጸሙ በፊት ስለአሟሟታቸው በሐኪሞች የተደገፈ ማስረጃ ግንኙት ያሰፈልግ ስለነበረ ዶ/ር ብላንክና የእጼ ቴዎድሮስ የንስሐ አባት በተገኙበት ዶ/ር ለምስደይን(25) አስከሬኑን መርምረው ያገኙት ውጤት «በጥይት የተመታ ቁስል ከበስተኋለ በኩል ጭንቅለታቸው ለይ ሲታይ፤ እንደዚሁም ከአፈቸው ውስጥ ጠቶር ብሎ ጉድጉድ ያለ ቁስል ይታይበት እንደነበረ፤ የሽጉጣቸውን እፈሙዝ ከአፈቸው አጉርሰው የተኩሱት ጥይት በአፈቸው ጣራ በኩል አድርጋ የኋለ ጭንቅለታቸውን አልፈ የወጣች በመሆኑዋ ንጉሡ ራሳቸውን በራሳቸው እንደገደሉ የሚመሰክር ነው በማለት አረጋገጡ።(26) የምርመራው ውጤት ከበቃ በኋለ ደክተር ኔንሪ ብለንክ እንደህ ብለው ተናገሩ። «ስሜቴን በጣም የቀሰቀሰው የሟቹ የቴዎድሮስ ራሰ ነበር።(27) የቴዎድሮስ ራሰ ፈገግ ብሎ ይታያል፤ የዚህ ዓይነቱ ደስታ የተመለከተ ፈገግታ ከእጼ ቴዎድሮስ በቅርብ ጊዜ በህይወታቸው ሰሉ አይታይቢቸውም ነበር። ይህም ሁኔታ ፀጥታ የተመለከተ ብዙ አስደናቂ ሥራዎችን ያከናወኑ፤ ታለቅነትና

ጨካኝነታቸውም በታሪክ ውስጥ ተወደደሪ የሌለውን የሰው ቅርጽ የያዘ በሕይወታቸው ማለፊያ ጊዜ የወጣትነታቸውን ወራት፤ በጀግንነት ያደረጉአቸውን ውጊያዎችና አሁንም ራሳቸውን በራሳቸው መገደለቸውን አስበው መደሰታቸውን ያሳያል።»

ምንም እንኪ ጄኔራል ናፒየር የእጼ ቴዎድሮስን ራሰ ለቀብር እንዲዘጋጅ ብሎ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም የት በታና በእንዲት ያለ ቀብሩ እንደሚከናወን ገና አልተወሰነም ነበር። ይህም ጉዳይ ለሚች ባለቤት ለእቴጌ ጥሩወርቅ በጥያቄ መልክ ቀርበለቸው ሲመልሱ(28) ግን በግል ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ» በማለት የተናገሩት በጀኔራል ናፒየር በኩል ተቀባይነት በማግኘት(29) የእጼ ቴዎድሮስ ራሰ በጉጆው ውስጥ እንደሰ በነጭ ጨርቅ እንዲጠቀለል ተደረገ።(30) ከዚያም በወርቀዘቦ ያሸበረቀ የሀገር ልብስ ከለበሰ በኋለ በአልጋ ለይ ተደርጎ ወደ ቀብር እመራ።(31) የእጼ ቴዎድሮስ የውስጥ ጠለቶች እደጋ ሊያደርጉበቸው ይችሉ በሚል ስጋት በለቤታቸው እቴጌ ጥሩወርቅና የሰበት ዓመት ሕፃን ልጃቸው ደጃዝማች ዓለማየሁ በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ለይ አልተገኙም ነበር።(32) ይሁን እንጂ የቅርብ ዘመደቻቸውና ጥቂት መኳንኖች በተገኙበት በሕይወታቸው ሰሉ መቅደሰ ለይ አሠርተውት በነበረው በመድሃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ፅሎት ተደርጉሎቸው ከአቡነ ሰላማ መቃብር አጠገብ(33) በተወሰደ በሃምሳ አመታቸው ሚያዚያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም. የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው ተፈጸመ።

ዘረፋ

እንደ እንግሊዝ ጦር አዛዦች አበባል ተልዕኮአቸው የእንግሊዝ አስረኞችን ለማስፈታት ነበረ። ከዚህ የተልዕኮ ሽፋን በስተጀርባ ግን ዓለማቸው እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ታሪክዊና በሀሳዊ ይዘት ያለቸውን ቅርሶች ለመዝረፍ ጭምር መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም።

፩ኛ ሪቻርድ ሆምስ የተበለው የብሪትሽ ሙዚየም ተወከይ ከእንግሊዝ ጦር ጋር አብሮ እንዲመጣ መደረጉ ለዚህ የዘረፋ ተግባር መሰከት እንደነበረ ግልጽ ነው።

ይኖ የእንግሊዝ ወታደሮች በቴዎድሮስ ራሳ ላይ የተረባረቡት ለምን ይሆን በግለት ራሳችንን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ምናልባትም ሰይማረኩ ራሳቸውን ገድለው በመገኘታቸው የተነሳ በእንግሊዘኞች በኩል የመበቀል ሁኔታ እንፀበርቆ ሊሆን ይችላል፤ በሰበቡ ግን ዘረፋ መፈጸማቸው አይከድም።

በቴዎድሮስ ገናናነትና አልበገር በይነት የተነሳ ካሁን አሁን ሽንፈት ይደርስብን ይሆናል በማለት የመንፈስ ጭንቀት ያደረባቸው የእንግሊዝ ወታደሮች የአጼ ቴዎድሮስን መዉረሽ እስከሳወቁ ድረስ ለዘረፋ ሊሰማሩ አልቻሉም ነበር። ውሎ አድሮ ግን ንጉሡ ራሳቸውን መግደላቸው በይፋ እንደተገለጸ ወደ ዘረፋ ተግበራቸው በቡድን በመሆን በየአቅጣጫው ተሠማሩ።

የመጀመሪያው የዘረፋ ቡድን ያተኮረው በሟቹ ንጉሥ ራሳ ላይ ነበር። የእንገት መስቀልና የጣት ቀለበታቸውን፤ ሽሚዛቸውንና ሽጉጣቸውን ከመዝረፋቸውም በሻገር ሹሩባቸውን ሰይቀር ሸልተው የወሰዱ ለመሆኑ በታሪክ መዛግብት መረዳት ይቻላል።

ሁለተኛው የዘረፋ ቡድን ያተኮረው የቤተመንግሥት ሕንጻ በመድረር ነበር። ንጉሡ በሕይወታቸው ሰሱ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ለማቋቋም የሰበሰቡአቸውን እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ መጽሐፍቶችን(34) እንደዚሁም በሠኑ ጊዜ የብሔራዊ ቤተ መዛግብት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ አያሌ የመንግሥት ሰነዶችንና የተለያዩ መረጀዎችን ሰይቀሩ ዘርፈዋል። ከነዚህም መካከል የአጼ ቴዎድሮስ ዘውደችና ማሕተም፤ በተለይም ከብረ ነገስት የተበለው ታለቁ መጽሐፍ ይገኙበቸዋል።(35) ቀጥለውም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ማድቤት ውስጥ በመግበት ወደ ሃያ እንሥራ የሚሆን የተጠመቀ ጠጅና የእህል አረቄ ዘርፈው ከመጠን በለይ ሰክረው ነበር። ከዘረፉአቸው ቅርሶች ይልቅ ጥፋት ያደረሱባቸው አመዝነው ታይተዋል። ብዙ ቅርሶች ጥለዋል፤(36) ሰባብረዋል፤ መጽሐፍትንም ቀደደዋል፤ አልባሰትንም ሸረከክተዋል።

የሦስተኛው የዘረፋ ቡድን ከወሰደቸው መካከል ከወርቅ የተሠራ የአቡነ ሰላማ አክሊል ወይም ዘውድ ሜግና ቀበቶ፣ ከወርቅ የተሠሩ ሁለት ጽዋዎች(37) ከወርቅ የተሠራ በእንገት ላይ የሚጠልቅ የአጼ

ቴዎድሮስ የሰሎሞን ኒሽን እንደዚሁም ንጉሠ ሲነገሠ ለብሰውት የነበረው የማዕረግ ልብስ ይገኙበቸዋል።

አራተኛው ቡድን ከዘረፋቸው መካከል የተለያዩ ጋሻዎች፣ ከነዚህም ውስጥ የአጼ ቴዎድሮስ ጋሸ ሰይሆን አይቀርም ተብሎ የሚገመተውና የፈታውራሪ ገብርዬ ጋሸ፣ ልዩ ልዩ ጦሮችና ጉራዴዎች፣ ያሸበረቁ የፈረስ ዕቃዎች፣ በተጨማሪም የቴዎድሮስ አስረኞች የታሰሩበት የእግር ብረት ይገኙበታል።

አምስተኛውና የመጨረሻው የዘረፋ ቡድን ያተኮረው አጼ ቴዎድሮስ በየእገሩ ሲዘዋወሩ ያርፉበት በነበረው ድንኳናቸው ይጠጡበት ወታደሮቹ በዚህ ሰይገቱ የደረሱበትን መንደር በግለስና እያንዳንዱ ቤት ውስጥ በመግበት ተመሰሳይ ዘረፋ ከግከሄዳቸውም ባሻገር ከተለያዩ ቤተክርስቲያኖች የተገኙትን መንፈሳዊ ስዕሎችና እንደዚሁም ቁጥራቸው አሥር የሚደርሱ ታቦቶችን(38) ሰይቀሩ ወስደዋል። በአጠቃላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ቤተመንግሥት ጀምሮ በእነስተኛ ጎጆ ውስጥ የሚገኙ ታሪከዊና በሕሰዊ ቅርሶች ሰይቀሩ ተዘርፈዋል።

አብዘኛዎቹ በዘረፋ ላይ ተሠማርተው የነበሩት ወታደሮች አስተሰሰብ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት እንጂ ለዕቃዎቹ ታሪከዊና በሕሰዊ ቅርስነት እንደልሰጧቸው መገመት እያዳግትም። ለምሳሌ፤ ሪቸርድ ሆምስ የብሪትሽ ሙዚየም ኤክስፐርትና አርኪዎሎጂስት ከእንድ በዘረፋ ላይ ተሰማርቶ ከነበረ ወታደር ከወርቅ የተሠራውን የአቡነ ሰላማን የዘውድ አክሊልና የወርቅ ጽዋ(39) በለዩ ላይ በግዕዝ እንደሚከተለው የተጻፈበትን «ዝንቱ ጽዋዕ ዘወሀብዋ ዳግማዊ ኢያሱ ወብእሲቱ ወለተ ጊዮርጊስ ለቅድስት ቁስቋም ከመ ትኩኖሙ መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ» ወደ አማርኛ ሰተረጉም እንዲሁም አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ለቁስቋም ቤተክርስቲያን ያበረከቷቸውን ሦስት ኪሎ የሚመዝኑ የቁርበን ጽዋዎች» መሰት ሲሆን እነዚህንም በእራት የእንግሊዝ ፖውንድ(40) ብቻ እንደሸጠሰቸው ይነገራል።

ጀኔራል ናፒየር የወታደሮቹን አስተሰሰብ መነሻ በማድረግ በመቅደላና በአከባቢዋ የተዘረፉት የበሕልና የታሪክ ቅርሶቻችን በሙሉ በጨረታ እንዲሸጡ ወሰነ።(41)

ጨረታውን የተሰካ ለማድረግ ገለጣ በሆነችው ደለንታ ሚደ እንዲከሄድ ተወሰነ። ቅርሶቹን ከመቅደላ ወደ ደለንታ ለማድረስ በእሥራ አምስት ዝሆኖችና ከሁለት መቶ በላይ በሚሆኑ አጋሰሶች ተጠቅመዋል።(42) ይህም የሚነግረን የቱን ያህል ብዛት ያላቸው ቅርሶች ተዘርፈው እንደነበረ ነው።

ደለንታ እንደደረሱም የተለያዩ ስጋጃዎች ሜዳው ላይ እንዲነጠፉ ተደረገ። በስጋጃዎቹ ላይ ቅርሶቹ በያይነታቸው ተደርድረው ለጨረታ ተዘጋጁ። አጫራችም የሚሆን መኮንን ተመረጠ። ለሽያጭም ከቀረቡት ዕቃዎች መከከል የአጼ ቴዎድሮስ ፀጉር ይገኝበት ነበር።

ጨረታው ከተጀመረ አንስቶ እስከለቀበት ጊዜ ድረስ በማንም ሊሸነፉ ያልተቻሉት ቀደም ሲልም ገና ከሀገራቸው ሲንቀሳቀሱ ገንዘብ አስታቅፈዋቸው ወደ ኢትዮጵያ ተሸኝተው የነበሩት የብሪትሽ ሙዚየም ተወካይ ሚስተር ሪቻርድ ሆምስና እንዲሁም ከወታደሮቹ በኩል ኩሎኔል ፍሬዘር ይገኙበታል። ለምሳሌ፣ አጼ ቴዎድሮስ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ይይዙት የነበረው በብርና በወርቅ ያሸበረቀ ጋሻ(43) የጨረታው መነሻ አስር ዶላር ሆኖ እስከ ሁለት መቶ ዶላር በመድረስ ኩሎኔል ፍሬዘር የጨረታው አሸናፊ በመሆን ሊገዛው ችሎአል።

ጨረታው ለሁለት ቀናት ያህል ከተከሄደ በኋላ ከሽያጭ የተሰበሰበውን አምስት ሺ ፖውንድ ወታደሮቹ እንዲከፋፈሉት ደተረገ።(44)

ምንም እንኳን ጀኔራል ናፒየር በዘዘው መሠረት በመቅደላ ተሰብስበው የነበሩት ሁሉ ቅርሶች ለጨረታ ቀርበው ነበር በግለት ለማስመለል ተሞከረ እንጂ አንዳንድ በለሃብቶች በተለይም ሲቪሎችና አፈሰሮች ራሱ ጀኔራል ናፒየር ለይቀር ቀደም ብለው ጨረታው በይፋ ከመጀመሩ በፊት ለየራሳቸው ያከማቹአቸው ቅርሶች በብዛት እንደነበሩ ድርጊቱ ካለፈ በኋላ ሊታወቅ ተችሎአል። ለምሳሌ ለጨረታው

ከልቀረቡት ቅርሶች መከከል የአጼ ቴዎድሮስ ዘውዶች፣ የማዕረግ ልብሶቻቸው፣ በሺ የሚቆጠሩ የብራና መጽሐፍቶችና የቴዎድሮስ ግህተም፣ የእቡነ ሰላማ የወርቅ አክሊል፣ በብር ያሸበረቀ ጋሻ፣ በክብረበዓል ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል የቴዎድሮስ ከበሮና የመሳሰሉት ከሌሎች ንብረቶች ጋር ከመቅደላ ቤተ ክርስቲያን አጥር ግቢ በነበሩት ጎጆዎች ውሰጥ ታምቀው(45) እንደነበር ይነገራል።

እንደዚህም ጨረታው ላይ ቅርሶቻቸውን ካለቀረቡት መከከል ጨዋ መስለው የሚታዩ፣ በዕድሜ በሰል ያሉና የተከበሩ፣ ቀደም ሲልም ለበኪዎች የነበሩ እውሮፖውያን ገና ወታደሮቹ በቡድን እየሆኑ ለዘረፋ ከመሰማራታቸው በፊት ሰርቀው ያስቀመጡአቸው ቅርሶች ከእገሮቻቸው አጠገብ ተከምሮ ይታይ እንደነበር እስታንሊ(46) አብራርቶ ገልጾታል። በተለይም ከእቡኑ መቃብር ላይ ተፈጽሞ የነበረውን የስርቆት ወንጀል አስመልክቶ ሲናገር «በጣም ከሚያስገርመውና ከሚያሰዝነው ነገር ሁሉ ከእስረኞቹ መከከል አንዱ ከስድስት ወር በፊት ተቀብረው የነበሩት ከእቡነ ሰላማ መቃብር ድረስ በመሄድ መቃብሩን አውጥቶና ሰብር ብዙ ሺ ዶላር ሊያወጣ የሚችል ከአልማዝ የተሠራ መስቀላቸውን ከእንገታቸው ላይ መንጭቶ መውሰዱ የቱን ያህል የተረገመ ሰይጣን እንደነበር ነው።» ሲል በዝርዝር አስቀምጦታል።(47)

ቀደም ሲል ለጨረታ ያልቀረቡ የቤተመንግሥት ንብረቶችና የጦር መሣሪያዎች ተቀምጠው ከነበሩበት ከመቀደላ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አጥር ግቢ ከሚገኙት ጎጆዎች ውስጥ(48) የአጼ ቴዎድሮስን የማዕረግ ልብስና ዘውዶቻቸውን፣ መጽሐፍታቸውን፣ ጽዋቸውንና ከበሮአቸውን እንደዚሁም ማሕተማቸውን ወደሀገሩ ለመውሰድ ለይቶ በማውጣት፣ የተረፉን ንብረት የወሎ በላባት ልጅ ለነበሩት ለወይዘሮ መስተዋትና ለወጣቱ ልጃቸው ለይማም ዓምደ(49) ከእስረከበ በኋላ ሰስት ሺ ቤቶች የሰፈሩበትን የመቅደላ መንደር እጼ ቴዎድሮስ የተቀበሩበት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ሰይቀር በእሳት በማጋየት(50) መቅደላን እንደለነበረች አደረጋት።

ይህንን ጦርነት በማስተባበር የተሰከ ውጤት ለሰገኙት የቴዎድሮስን ከበሮ ሦስት የተለያዩ ብርጌዶች ከሸለማቸው በኋላ፣ ሌሎቹን ቅርሶች አግበስብሰ ወደ አገሩ ተመለሰ።

ምንም እንኳ ጦርነቱ እንደበቃ የእንግሊዝ ወታደሮች ብዙ ሳይቆዩ ወደአገራቸው የተመለሱ ቢሆንም ለመንገዳቸው ከሚገለገሉባቸው ምግብና የቤት ቁሰቁሶች በሸገር እግረመንገዳቸውን፣ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ቅርሶቻችንን ከሀገር ለማስወጣት ሲሞክሩ በጉዘአቸው ላይ ሰሉ አያሌ መከራናስቃይ ደርሰባቸው እነደነበር በታሪክ ተመዝግቦአል። ለምሰሰ:- ጀኔራል ናፒየር በሱ የሚመሩት የጦር መኰንኖቹ እ.ኤ.አ. ሜይ 29 ቀን 1868 ከኢትዮጵያ ክልል ጠቅለለው ለመውጣት ወደ ሰንዓፈ አካበቢ እስከተቃረቡ ድረስ ሽፍቶች አልፎ አልፎ እደጋ ይጥሉባቸው ነበር። በየጊዜያቱ የሚጥለውም ዝናብ ጉዘአቸው እንዲሰናከል አድርጎባቸዋል። በተለይም አንድ ቀን የጣለው ኃይለኛ ዝናብ መንገደቸውን ሊዘጋባቸው ከመቻሉም በሰይ የማያቋርጥ ጎርፍ ሰለነበር ብዙ እንሰሳትና የሰባት ሰዎች ሕይወት ሊያልፍ ችሎአል።(51)

ታሪኩ በዚህ ብቻ አሰበቃም። የመቅደሰን ጦርነት እስከ መዉረሻው ድረስ ሲከታተል የነበረው ጋዜጠኛ በጉዘው ላይ አጋጥሞት የነበረው ስቃይ በቀለሉ የሚገመት አልነበረም። ይህ ግለሰብ በዉረታ የሰበሰባቸውን ቅርሶች በአምስት አግሰስ ጭኖ(52) ከመቅደሰ ወደ ሰንዓፈ ከዚያም ወደ ዙሰ በሚጊዝበት ወቅት እጅግ በጣም የማያቋርጥ ኃይለኛ ዝናብ በመዝነቡ የተነሰ ከየተራርቹ የሚወርደው ጎርፍ ወደ ጀረትነት፤ ከዚያም ወደ ወንዝነት እየተቀየረ በመምጣቱና የወንዙም ሙሰት ጊዜ በማይሰጥ ሁኔታ እየዉመረ በመሄዱ ጋዜጠኛውና ጊደኞቹ ተሰፈ ቶርጠው ከለቀለቻቸው በኋሰ ድንገት የዝናቡ መጠን በመቀነሱ ሕይወታቸው ሊተርፍ ችሏል።(53)

ስለሆነም በዝናቡ ኃይል እየተሸገሸገ ወደ ወንዙ የገባው የእሬር ደለል ከፍታ፤ እስከ አንድ ሜትር በመድረሱ አጋሰሰቹ ከተጫኑት የቅርስ ሸክም ጋር ይህንን ደለል ለማቋረጥ በለመቻሰቸው ጋዜጠኛውና ጊደኞቹ ያለውዱታቸውና ያለፍለጎታቸው ክብደት ለመቀነስ ሲሉ ብቻ ከበድ ያሉትን ቅርሶች እያወጡ ጥለዋቸዋል። ከነዚህም መከከል በደለንታው ዉረታ ላይ በሃምሰ ሩፒ (የህንድ ገንዘብ) ገዝቶ ያኖረው ዘጠና ኪሎ ክብደት ይመዝን የነበረው የቴዎድሮስ ስጋጃ ይገኝበታል።(54)

በመዉረሻም ጋዜጠኛው ይህንን ሁሉ ፈተናና ስቃይ አልፉዙለ ለይ ጭነዋቸው ያመጧቸውን ቅርሶች በሰጥን አስገብቶ ካሸጋቸው በኋሰ ተብለ በምትጠራው አነስተኛ መርከብ አሱና የአጼ ቴዎድሮስን እራት ሚልወርድ ጋር በመሆን በስዊዝ ከናል በኩል አድርገው ጉዘአቸውን ወደ እንግሊዝ አገር አመሩ።

የአቡነ ሰሰማን ከወርቅ የተሠራ አክሊልና የቁርበን ጽዋ ከአንድ ጦር ሜዳ ላይ ከዋለ ወታደር የብሪትሽ ሙዚየም ተወክዩ ሆልምስ በአራት የእንግሊዝ ፖውንድ ብቻ ገዝቶት እንደነበር ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ እንግሊዘኞች ድል አገኘን ብለው ወደ አገራቸው እንደተመለሱ የተጠቀሱትን ሁለት ቅርሶች ሪቻርድ ሆልምስ ከኩሎኔል ፍሬዘር፤ ከኩሎኔል ሚልወርድና ከኩሎኔል ካሜሩን ጋር በመመሰጠር «ዘ እቢሲኒያን ፕራይስ ፈንድ ከሚቴ» በሚል ስም ለብሪትሽ ሙዚየም በሁለት ሺ የእንግሊዝ ፖውንድ እንዲሸጥለቸው እ.አ.አ. ጁሰይ 1/1868 እቅርበውት እንደነበር የደብደቤ መረጃዎች ይጠቁማሉ።(56)

በሽያጭ ሆነ ወይም በስጦታ መተሰሰፋቸው ለጊዜው በይታወቅም በሁኑ ጊዜ ከመቅደሰ የተወሰዱት ቅርሶች በእንግሊዝ አገር ሙዚየሞች ውስጥ በእመጡእቸው ሰዎች ስም ተመዝግበው ይገኛሉ። ለምሰሌ ፍራንሲስከ አልቨሬዝ በጻፈው «ዘ ፕሬስተር ጆን» ተብሎ በሚጠራው መጽሐፍ መዉረሽ ሰይ ተርጊዎቹና አዘጋጆዎቹ ሀንቲንግፎርድና ቤክንግሃም እንደጠቀሱት በብሪትሽ ሙዚየም ውስጥ «ሆልምስ ኩሌክሽን» እየተባሉ የሚጠሩ አሥር ታቦቶች ከመኖራቸውም በሰይ ብዘታቸው ከእንድ ሺ በሰይ የሚደርስ የኢትዮጵያ የእጅ ጽሑፍ መጽሐፎች በተጠቀሰው ሙዚየም ውስጥ ተደርድረው ለሕዝብ ይታያሉ።(57)

በጠቃሰይ፤ የሀገሪቷ ሀብቶች በተለያዩ ሥፍራዎችና ሙዚየሞች ውስጥ በግለሰቦችም እጅ ጭምር የሚገኙ መሆናቸው መታወቅ አለበት። ይህ ሁኔታ የተጠቃለለ ኢንሽንተሪ ለመስራት እስቸጋሪ ያደርገዋሰ። ቢሆንም ጥረቱ መቀጠል አለበት።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Henry M. Stanley, Commassie and Magdala (London, 1874), p. 449

2. Ibid.

3. Ibid .

4. Ibid.

5. Markham, The Abyssinian Expedition (London, 1869) p. 352.

6. Shepherd, Campaign in Abyssinia (London, 1868) p. 266.

7. Ibid, p. 352.

8. Ibid, p. 353.

9. Stanley, p. 451.

10. Markham, p. 353.

11. Ibid , p. 353.

12. A. Moorehead, The Blue Nile (London, 1962) p. 106.

13. Ibid.

14. Stanley, p. 450.

15. Ibid, p. 450.

16. Ibid. p. 450.

17. Markham, p. 353.

18. Stanley, p. 450.

19. Stanley, p. 453.

20. Stanley, p. 459.

21. Stanley, p. 459.

22. Shepherd, p. 312.

23. Ibid, p. 313.

24. Markham, p. 354.

25. A. Rassam, Narrative of the British Mission to Theodore (London, 1869), p. 342, 360-1.

26. Ibid, pp. 342, 361.

27. H. Blanc, A Narrative of Captivity in Abyssinia (London, 1925), p. 244; ሄንሪ ብላንክ የቴዎድሮስ እስረኛ፤ ደቻው ወ/ሥላሴ እንደተረጎሙት ገፅ 262

28. H.M. Hozier, The British Expedition to Abyssinia (London, 1925) p. 244.

29. Ibid, p. 360.

30. Ibid, p. 360.

31. Ibid, p. 361.

32. Rassam, p. 342-360, 361.

33. Shepherd, p. 266.

34. Markham, p. 358; Stanley, p. 459.

35. Shepherd, p. 244.

36. Stanley, p. 455.

37. Shepherd, p. 268.

38. F. Alvarez, The Prester John of the Indies II (London, 1960) pp. 543-548.

39. Shepherd, p. 268.

40. Stanley, p. 458.

41. Shepherd, p. 286.

42. Stanley, p. 463.

43. Stanley, p. 470.

44. Ibid, p. 471.

45. Markham, p. 358; ተክለጻዲቅ መኩሪያ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፤ 1982) ገጽ 446.

46. Myatt, p. 165; Stanley, p. 456.

47. Myatt, p. 165; Stanley, p. 457.

48. ተክለጻዲቅ መኩሪያ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፤ 1982) ገጽ 446.

49. Shepherd, p. 269; ተክለጻዲቅ መኩሪያ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፤ 1982) ገጽ 446.

50. Markham, p. 368.

51. Shepherd, p. 346.

52. Stanley, p. 495.

53. Ibid, p. 501.

54. Ibid, p. 501.

55. Hozier, p. 244.

56. Stanley, p. 504.

57. Alvarez, pp. 543-48.



አዲ ቲዎድሮስ የተተበሩበት የመቅደሰው መድሐኒዓለም ቤተ ክርስቲያን በጊዜው የተነሣ ርተግራፍ



የመድሐኒዓለም ቤተ ክርስቲያን በእንግሊዞች እንደተቃጠለ። ሄነሪ ብሰንክ ከሳፈው መጽሐፍ የተወሰደ



እንግሊዞች ዘርፈው የወሰዱት ታቦት። ከራሰም መጽሐፍ የተወሰደ



ከመቅደሰ የተዘረፉ የቤተመንግሥት እና የቤተክርስቲያን አልባሰትና ፅታዎች ለንደን ከተወሰዱ በኋላ በኤግዚብሽን ሲታዩ። ለምንድ ኢሉስትሬ የተሰኘ ጋዜጣ ሰይ የወጣ።